# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2015/40*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

## አሜሪካ በምሥራቅ አፍሪካ ለንግድና ኢንቨስትመንት ድጋፍ ታደርጋለች

*አሜሪካ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአፍሪካ የንግድ ፕሮጀክት በኩል በአፍሪካ የዕድገትና የገበያ ዕድል ስምምነት (AGOA) አማካይነት 80 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት የወጪ ገበያ ዕድል አመቻቸች*

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ጥቅምት 10፣2008 ዓ.ም.፡-** በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ ከፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ጋር በመሆን ኦሪጅን አፍሪካ፡- የአፍሪካ የምርት መገኛና የፋሽን ሳምንት በተሰኘ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በምርት መገኛነትና በኢንቨስትመንት መዳረሻነት ለዓለም አቀፍ ሸማቾች የአልባሳት፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ ውጤቶችና የቤት ማስዋብ ዘርፎችን የሚያስተዋውቅ የንግድ ኤክስፖ ላይ ተገኝተው ድጋፋቸውን ገልጹ፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ( USAID) ድጋፍ ያደረገለት ይኸው የንግድ ኤክስፖ ዋና ዓላማው የምሥራቅ አፍሪካ ዲዛይነሮችንና አምራቾችን በማስተዋወቅ ወደ ቀጠናው የመዋዕለ ንዋይ ፍሰትን መሳብ ነው፡፡

ፕሬዚዳንት ኦባማ እ.ኤ.አ. በ2013 የአፍሪካ የንግድ ውጥን የተሰኘ መርሀ ግብር ያስጀመሩ ሲሆን፤ ዋና ዓላማው በአጠቃላይ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጠናም ሆነ በቀጠናው በሚገኙ ሀገራት መካከል የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር ነው፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል የተሰኘ በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የሚደገፈው ተቋም በዋናነት ንግድና ኢንቨስትመንትን በቀጠናው የማስፋፋቱን ሥራ ይሠራል፡፡ ማዕከሉ ከተመሠረተበት ከህዳር 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች፣ ሸማቾችንና በምሥራቅ አፍሪካ ያሉ ድርጅቶችን በማገናኘት 170 የሚሆኑ የማገናኘትና የማስተሳሰር ሥራዎችን ሠርቷል፡፡ በዚህም መልኩ በአፍሪካ የዕድገትና የገበያ ዕድል ስምምነት (AGOA) በኩል 80 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ምርት ወደ አሜሪካ እንዲላክ አድርጓል፡፡ ከዚህም ከ16 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚሆነው ምርት የተላከው ከኢትዮጵያ ነው፡፡ በአፍሪካ የዕድገትና የገበያ ዕድል ስምምነት (AGOA) አማካይነት የአሜሪካ መንግሥት የንግድ ውድድርን፣ የሥራ ዕድሎች መስፋፋትን፣ እንዲሁም ድህነት ቅነሳን በማበረታታት ላይ ይገኛል፡፡ በስምምነቱ መሠረት 6,400 የሚሆኑ ሸቀጦች ወደ አሜሪካ ከቀረጥ ነጻ ሊላኩ ይችላሉ፡፡

አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ ባደረጉት ንግግር፡-“የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት በአፍሪካ ያለውን የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ሁኔታን በሚመለከት ያለውን የግንዛቤ መዛባት ለመቀየር የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በመደገፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሆነውን የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰትን ለመሳብ ድጋፍ ሲያደርግ ኩራት ይሰማዋል” ብለዋል፡፡ አክለውም በአፍሪካ ታላቅነት እንደሚያምኑ አመልክተዋል፡፡

የምሥራቅ አፍሪካ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል ከግሉ ዘርፍና ከየሀገራቱ መንግሥታት ጋር በመተባበር የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅፋቶችን በዘላቂነት በማስወገድ ዙሪያ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም ለአፍሪካና ለአሜሪካ ድርጅቶች የገበያ ዕድሎችን በማስፋፋት፣ቅንጅቶችን በመፍጠር እንዲሁም በምሥራቅ

አፍሪካ በኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት በሚችሉባቸው መንገዶች ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራም ይሠራል፡፡

በአፍሪካ የዕድገትና የገበያ ዕድል ስምምነት ሥር የሚገኘው የምሥራቅ አፍሪካ የንግድና ኢንቨስትመንት ማዕከል በንግዱ ዘርፍ ስለሚያካሂዳቸው የአቅም ግንባታና የትስስር ዕድሎችን የማመቻቸት ሥራዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚቀጠለውን የድረገፅ አድራሻ ይጠቀሙ፡፡

###

###